# የሱዳን ብርጌድ ጦር
# በኢትዮጵያ መሬት ላይ እንዲሰፍር ሁኗል

**ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ**

**ሚያዝያ** 8 **ቀን** 2000 **ዓ.ም**. ( April 16, 2008 )

**ሚያዝያ** 1 **ቀን** 2000 **ዓ.ም**. ( April 9, 2008 ) **ባወጣነው መግለጫ ከሑመራ እስከ ጋምቤላ ያለውን** 1600 **ኪሎ ሜትር የድንበር መሬት ለሱዳን ለማስረከብ የካቲት** 2 **እና** 3 **ቀን** 2000 **ዓ.ም**. ( February 10 - 11, 2008 ) **የኢሕአዴግና የሱዳን መንግሥት ጣምራ መልዕክተኛ ቡድን በጎንደር ክፍለ ሃገር ታች አርማጭሆ ውስጥ ደለሎ በተባለው ቦታ ሌሊት ተገኝቶ አዲስ የድንበር ምልክቶች መትከሉንና የአካባቢው ሕዝብ በከፍተኛ ቁጣ በመነሳት የድንበር ምልክቶችን ነቃቅሎ እንደጣለ ፤ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ሕዝቡን ሰብስበው ጉዳዩን በውይይትና በሽምግልና ለመፍታት ሞክረው የአካባቢው ሕዝብ ግን « እኛ በርስታችና በመሬታችን ሽምግልና አንገባም » ማለት ሙከራውን እንዳከሸፈና ኢሕአዴግ ድንበሩን ለሱዳን መንግሥት ለማስረከብና የሕዝቡን ተቃውሞ ለመስበር ሲል የአግአዚ ጦሩን ሑመራና አብደራፊ አካባቢ እንዲሁም በመተማ አቅራቢያ ሽንፋ በተባለው ቦታ ማስፈሩን ገልጸናል።**

**በቅርቡ ከአካባቢው በደረሱን መረጃዎች መሠረት ፥**

1**ኛ/ ኢሕአዴግና የሱዳን መንግሥት ባደረጉት ምስጢራዊ ስምምነት መሠረት ሽንፋ ላይ ሰፍሮ የነበረው የኢሕአዴግ አግአዚ ጦር ቦታውን ለቆ ሲወጣ ፤ በምትኩ የሱዳን ብርጌድ ጦር ሽንፋና አካባቢው በመሥፈር ቦታውን ተቆጣጥሯል።**

2**ኛ/ ይኸው የሱዳን ጦር የአካባቢውን ለም መሬት በመቆጣጠር ፤ የአካባቢው ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በራሳቸው መሬት ከሽንፋ ወንዝ ውሃ እንዳይቀዱ ፣ ከፍቶቻቸውን እንዳያጠጡ ከልክሏል።**

3**ኛ/ ከዚህ ሁሉ በፊት የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት በድንበሩ አካባቢ ትላልቅ እርሻዎች ያላቸውን የሃገሬውን ገበሬዎች በምስጢር በመሰብሰብ ፤ የኢትዮጵያን ጥቅም በሚያስከብር ሁኔታ ከሱዳን ጋር ድንበሩን ለመካለል እንዲቻል በማለት ሱዳን ርዕሰ ከተማ ካርቱም ድረስ ወስደው በማያውቁት የእንግሊዘኛና የአረብኛ ቋንቋ በተዘጋጀ ሠነድ ላይ እንዲፈርሙ ተደርጓል። ይህ ከሆነ በኋላ ፤ እነዚሁ የሃገሬው ገበሬዎች እርሻዎቻቸው በሙሉ ለሱዳን ስለተሰጠባቸው አቤቱታ ቢያቀርቡ ተስማምተው እንደፈረሙ ተነግሯቸዋል። በዚህ የተነሳ ፤ ኢሕአዴግ በማያውቁት ቋንቋና ሁኔታ አታሎ እንዳስፈረማቸው በመግለጽ ለመለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪ በማቅረብ ላይ ናቸው። በዚህ ምክንያት በአካባቢው ከማንኛውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ ውጥረት ሰፍኖ ይገኛል።**

የአካባቢው ሕዝብ አሁንም ደግሞ ደጋግሞ በጥብቅ የሚያስገነዝበው ዳር ድንበሩን ለማስከበር በከፍተኛ ትግል ላይ ስለሚገኝ ፤ ከሱዳንና ከኢሕአዴግ አግአዚ ጦር በሚደርሰው የደም መፋሰስ ፣ የንብረት መውደምና የሕዝብ መፈናቀል የኢሕአዴግ መንግሥት ፣ በክልሉ ያሉት ባለሥልጣናትና የሱዳን መንግሥት በታሪክና በሕዝብ ተጠያቂ መሆናቸውን ነው።

የሱዳን መንግሥት ከሀገር ከሃዲውና ፀረ-ኢትዮጵያ ኢሕአዴግ ጋር በመመሳጠር በኢትዮጵያ መሬት ላይ ያሰፈረውን ጦሩን በአስቸኳይ እንዲያስወጣና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት እንዲያከብር የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች ፣ ሲቪክ ማህበራትና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሱዳን መንግሥት ላይ የተቃውሞ ድምጻቸውን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያሰሙ ፤ እንዲሁም የድንበር ጉዳይ ኮሚቴው በሚያደርገው እንቅስቃሴ ድጋፋቸውን እንዲሰጡ ኮሚቴው ወገናዊ ጥሪውን ያቀርባል።

የድንበር ጉዳይ ኮሚቴው የሁኔታዎችን እድገት በቅርብ በመከታተል ተከታታይ መግለጫዎችን የሚያወጣ መሆኑን ያስታውቃል።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በልጆቿ ይከበራል!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ